

# በብሪታንያ የምንገኝ ካህናትና ምዕመናን እንድንጠነቀቅበት

በዚህ ጾመ ማርያም (ፍልሰታ) ሱባዔ ውስጥ ለንደን በሚገኘው በርእሰ አድባራት ደብረ ጽዮን ማርያም ካቴድራል የተፈጸመውን አሳፋሪና ሕገወጥ ድርጊት ካህናትና ምዕመናን በትዝብት ብቻ እየተዋያዩበት ሰንብተዋል።

የደብሩ ካህናትና ምዕመናን ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ሕልውና ጠንቅ የሆኑትን ፓትርያርክ ጳውሎስን ስም በቅዳሴ ጊዜ ላለመጥራት በአስተላለፉው ጠንካራ መግለጫ ምክንያቶቹ በዝርዝር ተገልጠዋል። በተወሰደውም አቋም ምክንያት ከኢትዮጵያ እየተሾሙ የመጡትን ጳጳሳት ባለመቀበል አቋሙን ጠብቆ ቆይቶ ነበር። አሁን ግን ባልታወቀ ውስጣዊ ሴራ አባ መልከጼዲቅ የተባሉትን የአባ ጳውሎስን ዋና አቀንቃኝ ተቀብሎ፣

1. መቅደስ ገብተው እንዲባረኩ ፈቅዷል፣
2. በቅዳሴ ጊዜ ስማቸው እንዲጠራ አድርጓል፣
3. ባልተሾሙበትና መብታቸው በማይመለከተው ደብር የማዕረግ ስም እንዲሰጡ ተደርጓል፣
4. መድረክ ተሰጥቷቸው፣ በአባ ጳውሎስ የምትመራው ቤተክርስቲያን ከምንጊዜውም የበለጠ መብቷ እንደተጠበቀ፣ እና ከግራም ከቀኝም ምንም እንደማያሰጋት ቀደም ብሎ ከተላለፈው መግለጫ ፍፁም ተቃራኒ የሆነ ስብከት ነዝተዋል።

እኒህ አባ መልከ ዲጼቅ የተባሉ ጳጳስ የተሾሙት በሕገወጡ ፓትርያርክ አባ ጳውሎስ ሲሆን፣ በሕይወት ያሉትን የሕጋዊውን ጳጳስ አቡነ መልከ ጼዲቅን ስም ወስደው ነው። በአለፈውም በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ (ሕጋዊው ፓትርያርክ) በሚመራው ሲኖዶስ ከተወገዙትና በቀድሞ ስማቸው እንዲጠሩ ውሳኔ ከተላለፈባቸው ጳጳሳት አንዱ ናቸው።

ታዲያ ይኸ ሁሉ መሆኑ እየታወቀ፣ እኒህን ግለሰብ በርዕሰ እድባራት ደብረ ፅዮን ካቴድራል ማስተናገድና ከመብታቸው ውጭ እንዲፈነጩ ማድረግ የደብሩን አስተዳደር ያስጠይቃል።

ሕገ ቤተክርስቲያንን ከሚያውቁ ሊቃውንት ለመረዳት ስንጠይቃቸው፡

“በቤተክርስቲያን ሕግ መሰረት ለታላላቅ ገዳማት መምህራን፣ ለአድባራት አለቆች የማዕረግ ስም የሚሰጠው ፓትርያርኩ ወይም ለሀገረ ስብከቱ በሕግ የተሾመው ጳጳስ ወይም ሊቀ ጳጳስ ነው። አባ መልከ ጼዲቅ ግን አልፎሂያጅ እንግዳ እንጅ የደብረ ጽዮን

ጳጳስ አይደሉም። ለአለቃውም ሆነ ለሌሎች ካህናት የማዕረግ ስም መስጠት አይችሉም። የቤተክርስቲያን የማዕረግ ስም ሳይጠናና በሕግ ሳይፈቀድ እንደሰንበት ቂጣ ለዕገሌም ስጡልኝ እየተባለ የሚታደል አይደለም። ፈቃደኛ ያልሆኑትን መሪጌታ ዓለማየሁንም ጭምር በማዕረግ ስም ለማጥመድ የታየው ጨዋታ አሳፋሪ ነው። ስለሆነም የተሰጠው ስም ሕጋዊ ስላልሆነ ተዋናዩ ቀሞስ አባ ግርማም ሆኑ መሪጌታ ዓለማየሁ በዚህ ስም ሊጠሩ አይገባም።" ብለውናል።

የተፈጸመው ድርጊት በሰበካ ጉባዔውና በማሕበረ ካሕናት ተመርምሮ ለወደፊቱ ቀደም ብሎ በወጣው መግለጫ መሰረት ጠንካራ አቋም መውሰድ አለበት። ያለዚያ ምዕመናን የሚያዋጡት ገንዘብም ሆነ የቤተክርስቲያን ንብረትነት የሚዋልል አቋም ባላቸው አስተዳዳሪዎች አደጋ ላይ ሊወድቅ ስለሚችል ካሕናትና ምዕመናን ጉዳዩን በጽሞና ሊከታተሉት ይገባል። ሱባዔ ስለሆነ ካህናትም ሆኑ ምዕመናን ያሳዩት ትዕግስት ተገቢ ይመስለናል።

በሌላ በኩልም በተመሳሳይ ሴራ "ታላቅ መንፈሳዊ ጉባዔ በለንደንና አካባቢዋ" በሚል ርዕስ የተበተነው የስብሰባ ጥሪም በአባ ጳውሎስ ስር ከሚተዳደሩ አቀንቃኝ ካሕናትና መዘምራን የተዘጋጀ መሆኑን ያልተረዱ ካሉ ሊገነዘቡት ይገባል። ለዚህ ከፍተኛ ዝግጅት የሚዋጣውም ገንዘብ ከማን ኪስ እንደሆነ መረዳት አያዳግትም።

ለማደናገር "በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የምዕራብ አውሮፓ ሀገረ ስብከትና የለንደን ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን በመተባበር" ይላል። የማን ሐገረ ስብከት ነው? በማን ስር ይተዳደራል? ደብረ ገነት ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ማለት እኮ በርዕሰ አድባራት ደብረ ጽዮን ማርያም ካሕናትና ምዕመናን ውሳኔ፣ የአባ ጳውሎስ ስም በቅዳሴ ጊዜ እንዳይጠራ መግለጫ ሲወጣ አኩርፈው በሄዱት ጳጳስና ካሕናት የሚተዳደረው ነው። ከዚያም ከዚህ የሚሉ የዋህን ምዕመናንና ካሕናት ሕገቤተክርስቲያንን አክብረው፣ የሀገራቸውን ችግር ተረድተው አቋማቸውን ያለማወላወል ሊያጸኑ ይገባል። ቤተክህነትም ሆነ መንግስት እጹብ ድንቅ ስራ እየሰሩ ነው ብለው የሚያቀነቅኑትን ማዳመቅ ሀላፊነትን መዘንጋት ነው። በሃይማኖት ስም የሚጧጧፈው ንግድ መቆም አለበት። የሀገር ድንበር ሲፈርስ፣ ሕዝብ በርሃብ ሲጠበስ፣ ምንም ድምፅ ካማያሰሙ ደንታ ቢሶች ጋር ጊዜን ማጥፋት ያሳፍራል። ለዚህ ጉባዔ የሚተባበሩ የንግድም ሆኑ ሌሎች ድርጅቶች ከነማን ጋር እንደተሰለፉ ሊረዱት ይገባል።

በመግለጫውም፣ ለንደን የሚገኙት የአባ ጳውሎስ ጳጳስ አባ እንጦምስ፣ የተክለ ሃይማኖትን ጽላት በደባልነት ባርከው ያስገባሉ ተብሏል። አባ እንጦስ ማለት ሌላ ሳይሆኑ፣ ለርዕሰ አድባራት ደብረ ጽዮን ማርያም ካቴድራል በአባ ጳውሎስ ተሾመው መጥተው በሰበካ ጉባዔው እንዳይገቡ የተከለከሉ ሰው ናቸው። ያላወቃችሁ ወይም የዘነጋችሁ ካላችሁ ሴራውን ተረዱት።

ካሕናትና ምዕመናን አቋማችንን እናጽና፣ ነቅተን ቤተክርስቲያናችንን እንጠብቅ።

ከተቆርቋሪ ካሕናትና ምዕመናን።